በደቂቀ እስጢፋኖስ ሊገለጥ የነበረው የኢትዮጵያ አብርሆት (Enlightenment)- እጅግ የሚያስቆጭ ያመለጠን አጋጣሚና..

ኢትዮጵያ ባለፉት ፣ ሺህ ዐመታት ያመለጣት እጅግ የሚያስቆጭ ዕድል ደቂቀ እስጢፋኖስ ብፁዐን፣ የነቁ አባቶች በሐገረ-ኢትዮጵያ የእውቀት፣ የመገለጥና የአብርሆት ጮራ ሊፈነጥቁ በተነሱ ጊዜ በዘርአያቆብ ዐለም ላይ ያሉ የጭካኔ እርምጃዎች ሁሉ እንዲወሰድባቸው፣ እንዲገለደሉ፣ እንዲጠፉ ስለወሰነባቸው ነው።።

ደቂቀ እስጢፋኖስ ማእከላቸው ትግራይ ጉንዳ ጉንዶ አድርገው በተነሱ ጊዜ የነበረው አፄ አፄ ይስሐቅ (1406- 1421ዓ.ም) በገድላቸውና፣ በተአምራታቸው፣ በምጥቀታቸው ተደምሞ ሊጨክንባቸው አልፈለገም ነበር፤ እንደውም አወድሷቸው ነበር።።



ከሱ ሕልፈት በኃላ የተነሳውና የስለት ልጅ የነበረው፣ በገዳምም ያደገው አጼ ዘርኣ ያዕቆብ (1426-1460) በአንድ በኩል እውቀትን አክባሪ ሆኖ ሳለ በደቂቀ እስጢፋኖስ ግን እጅግ ጨከነባቸው።። በአባ አስጢፋኖስ፣ በተከታዮቻቸው የወሰደው እጅግ ጭካኔ የተሞላበት ስቃይና ግድያ የኢትዮጵያ ገዢዎች የጭካኔ ጠርዝ ምን ድረስ ሊደርስ እንደሚችል አመላካች ነው።።

ደቂቀ እስጢፋኖሶች በእምነታቸው የፀኑ፣ የሰው ልጅ በመንጋ አስተሳሰብን ሳይሆን በእውቀትና በሕገ-ልቦና እንዲመራ የሚያምኑ፣ በሐይማኖታዊ እውቀታቸው እጅግ የመጠቁ፣ የሰው ልጅ ከፈጣሪ ውጨ ለማንም ማጎንበስ የለበትም ብለው የሚያምኑ ነበሩ።።

በተለይም የአባ አስጢፋኖስ፣ አባ አባከረዙን፣ አባ ዕዝራ ሞገሳዊ መንፈሳዊ ጥንካሬ፣ የዐለማ ፅናት፣ የእውቀት (ሃይማኖታዊና ሳይንሳዊ) ምጥቀት እጅግ አሰደማሚ ነበር።። ያንን ተጠቅመን መስፈንጠር እየቻልን አጠፋናቸው፣ ቁልቁል ማዝገሙን መረጥን።።

ስለትግራይ በጎ መፃፍ የማይሆንላቸው ፕሮፌሰር መስፍን እንኳ በዶክተር ጌታቸው ሐይሌ “ደቂቀ እስጢፋኖስ” መፅሐፍ መግቢያ ላይ ደቂቀ እስጢፋኖስን ሲያወድሱ “ከሰዎች ፊት ከስልጣኔ በራፍ ላይ ደርሰን ከኃላችን የመጡ አልፈውን በአደራሹ ሲገቡ እኛ አሁንም ከውጭ ቆመን መቅረታችንና በልመና

የምንኖር መሆናችን የገዢዎቻችን የዐፈና ተግባር የማይቀር ውጤት ሆኖ ነው፡፡ በታሪካችን ሑሌም በሕገ-አራዊት እየተመራን፣ የሰውነት ሐብታችንን፣ አዕምሮአችንና መንፈሳችንን ታፍነን ኑሮአችንን የምናሻሽልበት ዘዴ ለመፍጠር አልቻልንም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ መንፈሳዊ ወኔ የነበራቸውና ሐሳባቸውንና እምነታቸውን ማንንም ሳይፈሩ በአደባባይ ለማውጣት የቻሉ እንደነደቂቀ እስጢፋኖስ የመሳሰሉ መገኘታቸው ከአፈናው ባሻገር ጭራሽ ባዶ አለመሆናችንን ያሳየናል” ይላሉ፡፡

የደቂቀ አስጢፋኖስ ስምና ዝና ገኖ፣ ሕዝቡ በነቂስ ሲቀበላቸውና በርካታ ተከታይ ሲያፈሩ አፄ ዘርአ-ያቆብ በነዚሁ አባቶችና በተከታይ ሕዝብ ላይ (በተለይም በትግራይ ሕዝብ ላይ) እጅግ አሰቃቂ ፍጅት ተፈፅሟል፡፡ እነ አቡነ ተክለሃይማኖትም የዚሁ ፍጅት ዋና ተዋናይ ነበሩ፡፡ ዶ/ር ጌታቸው ሐይሌ በነዚሁ ቅዱሳንና የነቁ አባቶች ስራ፣ ተጋድሎ፣ የደረሰው የግፍ መጠንና መጨረሻቸው ዙርያ የፃፉት መፅሐፍ ሳነብ በአንድ በኩል ያመለጠንን ዕድል አስባለሁ፣ በሌላ በኩል የመሪዎቻችን ጭካኔና የደረሰው ፍጅት አስባለሁ፡፡ ሁሉም እጅግ የሚያስቆጭ ነው፡፡

የደቂቀ አስጢፋኖስ መነኮሳት ከአፄ ዘርአያቆብ ጋር ያላስማሟቸውና በአፄው እንዲጠፉ ያስወሰኑባቸው የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው፤

- “ከፈጣሪ ውጪ ለማንም ማጎንበስ፣ መስገድ ስሕተት እንደሆነ” ያምኑ፣ ያስተምሩ ነበር፤ ለንጉሱ ለማገንበስም ፍቃደኛ አልነበሩም፤ ማርያምም ሆነ ሌሎች ቅዱሳት፣ መላዕክትም ቢሆኑ ሊከበሩ ሊዘከሩ እንጂ ሊሰገድላቸው እንደማይገባ ያስተምሩ ነበር፤
- “ሐይማኖትና መንግስት መለያየት አለባቸው” ብለው ያምኑ ስለነበር፤ በተለይም አፄ ዘርአያቆብና ከፊት የመጡ ነገስታት ከአንዳንድ ሐይማኖቱ መሪዎች ጋር በመሻረክ (ለአብነት ከአቡነ ተክለሃይማኖት ጋር) ቤተ-ክርስትያኒቱ የንጉሱ የሕዝብ ግንኙነት ክፍል እንድትሆን፣ ቤተ-ክርስትያንና ገደማትም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያገኙ የፈፀሙት ሻጥር (“ሲሶ ለነጋሽ፣ ሲሶ ለአራሽ፣ ሲሶ ለቀዳሽ” የሚለውን አዋጅ) በፅኑ ተቃወሙ፣ ሑሉም ሰርቶ ጥሮ-ግሮ መብላት እንዳለበት መፅሐፍ እንደሚስተምር ተከራከሩ፤ በዚህም ንጉሱና ጥቅም ፈላጊ የሐይማኖት አባቶች ጥርስ ነከሱባቸው፤
- “ለእንጨት መስቀልና ለስዕል ማጎንበስ የለብንም” ብለው ያምኑ ስለነበር፤
- “የአፄ ዘርአ የዕቆብ ደብተራዎች የፃፉትን ተአምረ-ማርያም ብዙ እንከን ያለበትና ተቀባይነት የሌለው ፀረ-ክርስትና ነው” ብለው ያምኑ ስለነበር፤
- ደቂቀ እስጢፋኖሶች ከሀይማኖታዊ ምጥቀት በተጨማሪ ከፍተኛ የሳይንስ እውቀትም አዳብረው ስለነበር፤

ብዙዎቹ እነዚሁ የደቂቀ አስጢፋኖስ ሐሳቦች ማርቲን ሉተር ኪንግ ከ30 ዐመት በኃላ ተነስቶ ከዐለም አስተጋብቷቸዋል፡፡ በፕሮቴስታኒዝምና በደቂቀ እስጢፋኖስ መካከል መሰረታዊ የነገረ-መለኮት የትርጓሜ ልዩነት እንዳለ ግን ሳንዘነጋ ነው፡፤

ደቂቀ እስጢፋኖስ በተለይም በሳይንሱ ረገድ ከፍተኛ ምጥቀት አሳይተው ነበር፤ ላቅ ያለ የአብርሆት (enlightenment) ጮራም በሐገራችን ሊፈነጥቁ ነበር፡፡ ምን ዋጋ አለው፣ አጼ ዘርአ ያዕቆብ አጠፋቸው፡፡

በሳይንሱ ረገድ ደቂቀ አስጢፋኖስ፤

- በዐለም ለመጀመርያ ጊዜ ሁለት ተክሎችን በማዳቀል አዲስ ተክል (hybride) መፍጠር የቻሉ ናቸው- ብርቱካንና አንድ እስካሁን ያልተደረሰበት ተክል በማዳቀል እጅግ ጣፋጭ የሆነ፣ግን ደግሞ ብርቱካንነቱ ያላጣ ፍሬ መፍጠር ችለዋል፤ ብርቱካኑ አሁን እየጠፋ ያለ ቢሆንም መቐለ ውስጥ “የጉንዳጉንዶ ብርቱካን” በመባል ይታወቃል፤
- በዐለም የመጀመርያው በነፋስ ሐይል የሚሰራ የውሐ መዘውር ሰርተዋል፤
- በውሐ ሐይል የሚንቀሳቀስ የእህል ወፍጮ ማሽን ሰርተዋል፣
- አስገራሚ የእርሻ ጥበቦች፣ ትልልቅ ውሐ ማስተላለፍያ ድልድዮችና ትቦዎች መዘርጋት ችለዋል፤
- እስካሁን በምርምር ሊደረስበት ያልቻለ በራሪ ማሽንም ሰርተው ነበር፤

ከነዚሁ የደቂቀ እስጢፋኖስ የምርምር ውጤቶች የተወሰኑቱ ከሁለት መቶ ዐመታት በኃላ እንግሊዞች ድጋሚ ፈጥረዋቸው የዐለም የኢንዳስትሪ አብዮትም (industrial revolution) መነሻም ሆኑ:: እንግሊዞቹ ሐሳቦቹን ከነዚሁ የጉንዳጉንዶ የደብረዳሞ አባቶች የወሰዱት ይሁን ወይስ የነገሮች መገጣጠም፣ እሱ ለታሪክ ተመራማሪዎች የሚተው ነው::

ባለፉት 1000 ዐመታት የደቂቀ እስጢፋኖስ የመከነ የአብርሆት (enlightenment) አብዮትን የሚስተካከል ያመለጠን መልካም አጋጣሚ መኖሩን እጠራጠራለሁ:: ቢሆንም ግን ከነደቂቀ እስጢፋኖስ በኃላ ሌሎች ምጡቃን የአብርሆት ጮራ ፈንጣቂዎች አልታዩም ማለት አይደለም:: ምሳሌዎች ብናነሳ ፈላስፋው ዘርአ ያዕቆብ (ንጉሱ አይደለም)፣ የኢኮኖሚክስ፣ የሕክምናና የማሕበራዊ አገልግሎት (social service) ሊቁ ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ወ.ዘ.ተ እናገኛለን:: ምን ዋጋ አለው፣ ሁሉንም አልተጠቀምንባቸውም ብቻ ሳይሆን በተለይም ከዘመኑ በሁለትና ሶስት መቶ ዐመታት ወደፊት ቀድሞ ያለዘመኑ የተወለደውና የአብርሆት ጮራ ለኢትዮጵያ ሊፈነጥቅ ሲተጋ የነበረው ነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ ገና በለጋ ዕድሜው በ32 ዐመቱ ልበ-ብርሐንነቱና ትጉህነቱ ጠላት አብዝቶበት የቤተ-መንግስት ሰዎች መርዝ ሰጥተው በአጭሩ እንዲቀጭ ሆኗል:: እጅግ ያስቆጫል! በቃ እንዲህ ነን፤ ልሩጥ ያለውን ጉልበቱ ማለት፣ መከርሸም፤ ወጣ ያለውን መኮርኮም፤ ረዘም ያለውን መቅጨት፤ ባለራዕዮችን፣ ጠቢባንን ማኮላሸት!

የኛ ትውልድ ስለደቂቀ እስጢፋኖስ ብዙ ለማወቅ መትጋት አለበት:: የደቂቀ እስጢፋኖስ ታሪክ የሰው ልጅ ለዕምነቱ፣ ለዐላማው ምን ያህል ሊፀና እንደሚችል ማሳያ ነው:: ከዚህም አልፎ የደቂቀ እስጢፋኖስ ታሪክ ልብህን ማድመጥ፣ ከመንጋው ተነጥለህ እራስህን ስለመሆን ያስተምረናል:: ከዐለም በብዙ ደቅመው በሳይንሱ በኩል ደርሰውበት የነበረው የምጥቀት ደረጃ ስታስብ፣ ከኛ በብዙ መቶ ዐመታት ዘግይተው የኢንዳስትሪ አብዮት የጀመሩት የአውሮፓ ሐገሮችና እኛ አሁን ያለንበትን ሁኔታ ስታጤን፣ በበዙ መልኩ ያስቆጫል::

ዘፅአት- ከመቐለ 06-19-17